አንባቢዬ ሆይ ጊዜህ በምን ሁኔታ እያለፈ ነው? ለጊዜው መልካም በሚመስሉ የኋላ ኋላ ግን መዘዝን በሚያስከትሉ ሁኔታዎች ላይ ይሆን ቀንህን የምታጠፋው? አስተውል ፈጣሪህን እግዚአብሔርን ረስተህ የምትዘፈቅበት ማንኛውም ነገር ለጊዜው ለስጋህ እርካታ ቢሰጥህም ነፍስህን ወደ ጥፋት ይወስዳታል።

ህይወቱን ለአንተ ሲል በመስቀል ላይ አሳልፎ የሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፦

“ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል? የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል።”
ማቴ.16፡26-27

በእግዚዓብሔር የፍርድ ዙፋን ፊት ለመቆም የሚያስችል ምን መልካም ሥራ ይዘሃል? ቀናቶችህ ለህይወት በማይበጁ ለጊዜያዊ ብቻ ሥጋዊ ስሜትን በሚያረኩ ከንቱ ልፋቶች እያለፉ ከሆነ በእውነትም ከእግዚአብሔር ፍርድ አታመልጥም። መጨረሻህም የእሳት ባህር ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር በፍርድ ሲገለጥ ወይም ደግሞ አንተ ከዚህች አለም ተሰናብተህ ወደ ዘላለማዊው መኖሪያህ መሄጃህ ሲደርስ በፈጣሪህ ፊት ድፍረት እንዲኖርህ አኗኗርህን አስተካክል። በኑሮህ ኢየሱስን አስቀድም። ክርስቶስን ወደ ህይወትህ በመጋበዝና በእርሱ በመኖር ለዘላለም ህይወት የሚያዘጋጅህን ተግባር መፈጸሙን ከአሁኑ ጀምር። የሚበጅህ ክርስቶስ ብቻ ነው። ስለዚህም ቀነ ቀጠሮ ሳታበዛ ዛሬውኑ ህይወትህን ለክርስቶስ ስጠው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሚበጅህን ያሳይሃል። ከንቱ ልፋትን ከህይወትህ አስወግዶ ደስ ወደሚያሰኝ ጎዳና ይመራሃል። በእርሱ ዘንድ ግራ መጋባት የለም።

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑበትን በከንቱ አይተዋቸውም። ይህን የተስፋ ቃል በእምነት ተቀብለህ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ልብህ ብትጋብዘው የዘላለምን ህይወት ታገኛለህ።

**“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።”**

ቀደም ሲል የተገለጹትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች አንብበህ በእውነትም ልብህን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ፈቃደኛ ከሆንክ የሚከተሉትን እርምጃዎች እንድትወስድ አደፋፍርሃለሁ።

1. አመቺ ጊዜንና ስፍራን በመፈለግ በጉልበትህ ተንበርከክና የሚከተለውን ጸሎት አድርግ፦

   “ጌታ ሆይ ከኀጢአቴና ከከንቱ ልፋቴ ተመልሼ ከአንተ ጋር አዲስ ጅማሬን ለመጀመር እፈልጋለሁና እባክህን ኀጢአቴን ይቅር በለኝ፤ ወደ ልቤም ግባ የዘላለምንም ህይወት አጎናጽፈኝ። አንተ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ አምናለሁ። እንደግል አዳኜም እቀበልሃለሁ፤ አሜን”

   ከዚህ በተጨማሪ ለጌታ ልታዋየው የምትፈልገው ምስጢር ካለህ ያደምጥሃልና ንገረው።

2. ከዛሬ ጀምሮ በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስህን ለማንበብና ለመጸለይ ውሳኔን አድርግ። በልብህም የሞላው የተለያየ ተስፋ መቁረጥ ስፍራውን ለክርስቶስ እየለቀቀ ይሄዳል።

3. እግዚአብሔርን በእውነት የሚያመልኩ ክርስቲያኖችን በመፈለግ ከእነርሱ ጋር ህብረትን ለማድረግ ወስን። በህይወትህ ያየኸውን ለውጥ ግለጽላቸውና ቅረባቸው፤ ወደ አንተም ጋብዛቸው። አሁን የተቀበልከውን አዳኙን ኢየሱስን የሚከተሉ ብዙ ወንድሞችና እህቶች አሉህ። ከእነርሱ ጋር ህብረትን እንድታደርግ የጌታ ፈቃድ ነው።

ስላደርግኸው ውሳኔ እግዚአብሔር ይባርክህ። ከእንግዲህ የክርስቶስ ልጅ ነህ እንጂ ዘመኑን በከንቱ የሚያባክን ተስፋ ቢስ ሰው አይደለህም። ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንኳን መጣህ!! በዚህ አድራሻ አግኘን

www.operationezra.com

# ከፀሐይ በታች ያለ ከንቱ ልፋት



“የዘመኖቻችንም ዕድሜ ሰባ ዓመት ቢበረታም ሰማንያ አመት ነው” መዝ.90፡10 በዚህ አጭር የእድሜ ዘመኑ ሰው ጊዜውን በምን እንደሚያጠፋው ወሳኝ ጉዳይ ነው። በቅርቡ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚነግረን በዚህ የሰባ ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚኖረ ሰው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከሚሞትበት ቀን ድረስ ያደረጋቸው ነገሮች ለብቻቸው ተሸንሽነው ሲደማመሩ የሚከተለውን ይመስላሉ።

አንድ ሰው ከተወለደ ጀምሮ እስከሚሞት ድረስ በመኝታ የሚያሳልፈው ጊዜ ሲደመር 23 አመታት ሲሆን በየዕለቱ በስራ ላይ የሚያቃጥለው ሰዓት ደግሞ ተጠረቃቅሞ የህይወቱን 18 አመታት ይዞ ይሄዳል። ከዚህቸው ካለችው አጭር ዘመን ቴሌቪዢን ለማየት የሚያሳልፈው ጊዜ በድምሩ 8 አመታት፣ ራሱን ለማሰማመርና ለማቆነጃጀት የሚያቃጥለው ጊዜ በድምሩ 7 አመት ተኩል፣በመመገብ የሚያሳልፈው ጊዜ 6 ሰዓታት ይሆናል። በተጨማሪም ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የሚያባክነው ጊዜ በድምሩ 6 አመታት ሲሆን፤ በህይወቱ ዘመን እግዚአብሔርን በማምለክ የሚያሳልፈው ጊዜ ተደምሮ 1 አመት ተኩል አይበልጥም።

ይህ ጥናታዊ ገለጻ አንድን ጥያቄ ራሳችንን እንድንጠይቅ ይጋብዘናል።

ጊዜያችንን የምናጠፋበት ነገር ምን ያህል አስፈላጊ ነው? ከጥናቱ እንደምንገነዘበው ሰው ብዙውን ጊዜውን የሚያባክነው ዘለቄታ በሌላቸው በስጋዊ ጉዳዮች መሆኑ ግልጽ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የምንለፋባቸው ነገሮች ብዙም የማይጠቅሙ ስለሆኑ እንዲሁ ጊዜአችንን ከማባከን በስተቀር ሌላ ትርፍ አናገኝባቸውም።

ይህን እውነት ጠቢቡ ሰለሞን ከብዙ ሺ አመታት በፊት በሚገባ በመገንዘቡ በአለም ተደናቂነት ባተረፈው ጽሑፉ ጠቃቅሶት አልፏል። ጠቢቡ ሰሎሞን የሰውን ከንቱ ልፋት አስመልክቶ ለሚሰማው ሁሉ ለማስተላለፍ የፈለገው ፍሬ አሳብ በሦስት ይጠቃለላል።

1. ከፀሐይ በታች የሚደክምበት ድካም ሁሉ ከንቱ ነው።

*“ሰባኪው። ከንቱ፥ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው ይላል። ከፀሐይ በታች የተሠራውን ሥራ ሁሉ አየሁ እነሆም፥ ሁሉ ከንቱ ነው፥ ነፋስንም እንደ መከተል ነው።” መክብብ 1፡2፤14*

አንባቢ ሆይ በዚህች ባለችህ አጭር የእድሜ ዘመን ጊዜህን በምን እያባከንከው ነው? ከዚህ በፊት የለፋህበትና አሁን እየደከምክበት ያለው ነገር ሁሉ ከልብ ጠብ እንደማይልና እርካታ እንደሌለው እስካሁን ሳትገነዘብ የቀረህ አይመስለኝም። ጠቢቡ ሰሎሞን አልተሳሳተም። በዚህች ምድር ላይ ሳለን ለእኛ ለሰው ልጆች የሚያረካን ምድራዊ ነገር ፈጽሞ አይገኝም።

ምናልባት የጀመርከውና ለረጅም ጊዜ የለፋህበት ሁኔታ መጨረሻው አላምር ብሎህ አዝነህ ይሆን? የምታደርገው ሁሉ እጅ እጅ ብሎህ ከአንዱ ተግባር ወደ ሌላው በመዘዋወር ጊዜህን እያባከንክ ይሆን? “በዚህ ምድር ላይ ውስጤን ሊያረካ የሚችልና ለዚያ ተግባር በመሰለፌ እርካታ ላገኝበት የምችለው ሁኔታ ምንድነው?” እያልክ ራስህን ጠይቀህ ይሆን? ዓላማ ቢስነት ይሰማሃል? ለእነዚህ ዘወትር ከአዕምሮህ አልወጣ ላሉ ጥያቄዎችህስ በቂ መልስ የሚሰጥህ ሰው አጥተህ ይሆን?

ለእነዚህ ጥያቄዎች ያለህ መልስ “አዎን” ከሆነ ለህይወትህ አዲስ ተስፋንና ደስ የሚያሰኝ ጅማሬን ሊሰጥህ የሚቻለውን አንድ ድንቅና አስገራሚ ሰው ላስተዋውቅህ። ይህ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ይባላል። አንተም ብዙም ስለ እርሱ ምናልባት እምብዛም አታውቅም ይሆናል እርሱ ግን አንተነትህን ጠንቅቆ ያውቅሃል። እንደውም ከእናትህ ማህጸን ሳትፈጠር ያውቅሃል።

ስለእርሱ ሲነግርህ ካለህ የራስህ አቋም የተነሳ ብዙም ፍላጎት ስታሳይ አልፈህ ሊሆን ይችላል፤ እርሱ ግን ያንተ ነገር አይሆንለትም። ስለአንተ መስማት ብቻ ሳይሆን ከአንተ ጋር መነጋገርን ይፈልጋል። አንተ አታየውም እርሱ ግን በዚህች ሰዓት እንኳን እያየህ ነው።

እንደውም ይህችን ለእርሱ ክብር የተጻፈች ጽሁፍ በእጅህ እንድትገባና እንድታነባት ሁኔታዎችን ያመቻቸልህ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ልብህን ብትከፍትለትና ወደ ህይወትህ ብትጋብዘው ወደ አንተ ለመምጣት አንዲት ደቂቃ አያባክንም። ክርስቶስ ወደ ህይወትህ ከገባ በኋላ ዓላማ ቢስነት ቀርቶ ዓላማ መር ህይወት ይኖርሃል። የምትሰራው ሁሉ በውስጥህ እርካታን ከመስጠቱም በላይ ይከናወንልሃል። ክርስቶስን የህይወታቸው ዓላማ ስላደረጉ ሰዎች ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያበረታታቸዋል፡-

*“በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና፤” ፊል.1፡6*

በክርስቶስ ትርፍ እንጂ ኪሳራ የለም። ከፀሐይ በታች የሚደክምበት ድካም ከንቱ ከመሆኑም በላይ . . .

2. ከፀሐይ በታች ከደከምንበት ነገር ከሞት ወዲያ አንዳች ይዘን አንሄድም።

*“ከእኔ በኋላ ለሚመጣው ሰው እተወዋለሁና ከፀሐይ በታች የደከምሁበትን ሁሉ ጠላሁት። ጠቢብ ወይም ሰነፍ እንዲሆን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? ከፀሐይ በታች በደከምሁበትና ጠቢብ በሆንሁበት በድካሜ ሁሉ ላይ ጌታ ይሆንበታል ይህም ደግሞ ከንቱ ነው።” መክ.2፡18-19*

ይህ አስገራሚ እውነት ነው። ሰው በዚህች ምድር ላይ ሲመላለስ ሳለ በብዙ ድካምና ጥረት የገነባቸውንና ያካበታቸውን ነገሮች ቀኑ ደርሶ ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ ሁሉንም ትቶ ይሄዳል። ይህም ሰው የደከመበትን ቅርስ ሁሉ የሚወርሰው ሌላው ሰው ነው። በተዘዋዋሪ መንገድ ሰው የሚለፋውና ላቡን ጠፍ አድርጎ የሚሰራው ለሌላው ሰው ትቶ ለመሄድ ሲል መሆኑ ነው። በዓለም ያለ ሁሉ ጠፊ ነው። ዛሬ ውብ ሆኖና አምሮበት ያየነው ሰው ነገ በመቃብር ውስጥ ይገኛል። በምድር ላይ ያካበትነውን ሃብት መቼ ተለይተነው እንደምንሄድ አናውቀውም። ይህ እጅግ በጣም ተስፋ የሚያስቆርጥ አሳብ ነው።

የምንኖርባት አለም ተለዋዋጭና ወረተኛ ናት። ዛሬ ያቀፈችውን ነገ ትገፋዋለች፤ ዛሬ ያከበረችውን ደግሞ ነገ ታወርደዋለች። በዚህ ዓለም ያለ ነገር ሁሉ ጊዜያዊ ነው። ለዘላለም አብሮን አይኖርም። ታዲያ እውነቱ እንደዚህ ከሆነ ሰው ለዘላለም ከእርሱ ጋር ለማይዘልቅ ነገር መድከሙ ለምንደው? ለመሆኑስ እስከ ዘላለም የሚዘልቅ ምን ነገር አለ?

ለዚህ ጥያቄ ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ የሚል መልስ አለው፡-

*“ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።” 1ዮሃ.2፡17*



እንግዲህ ምስጢሩ እዚህ ላይ ነው። አንድ ሰው ዘለቄታዊ የሆነን ነገር ማከናወን ከፈለገ ዘላለማዊ ወደ ሆነው አምላክ ሊጠጋ ይገባዋል። ይህንንም ለማድረግ የህይወት በር የሆነውን ክርስቶስ ኢየሱስን ወደ ልቡ በመጋበዝና በመቀበል ነው። ይህ መንገድና እውነት ህይወትም የሆነው ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ጨምሮ ይመክረናል፡-

*“ብልና ዝገት በሚያጠፉት*
*ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ*
*በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ነገር ግን ብልም ዝገትም*
*በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ*
*በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤መዝገብህ ባለበት ልብህ*
*ደግሞ በዚያ ይሆናልና።” ማቴ.6፡19-21*

ወገኔ ሆይ ዘላለማዊና ዘላቂነት ያለውን ነገር ከፈለግህ ወደ ክርስቶስ ተመለስ፤ ህይወትህን ስጠው፤ልብህን አስገዛለት። ያን ጊዜ የሚያስጨንቅህ ሁሉ ይቆረጥና ጊዜያዊ የስጋ ስሜትን ለማርካት ከመሮጥ ይልቅ ዘላለማዊ ህይወትን ለማትረፍ እንድትችል ዓይኖችህ ክርስቶስን ማየት ይጀምራሉ።

አዎን! ፀሐይ በታች ከደከምንበት ነገር ሁሉ አንዲቷም እንኳ ከሞት ባሻገር ተከትላን አትሄድም። ከዚያም በተጨማሪ . . .

3. ከጸሃይ በታች ባለችን አጭር ዘመን የሚበጀንን አናውቅም።

“ሰው በከንቱ ወራቱ ቍጥርና እንደ ጥላ በሚያሳልፈው ዘመኑ በሕይወቱ ሳለ ለሰው የሚሻለውን የሚያውቅ ማነው? ወይስ ለሰው ከፀሐይ በታች ከእርሱ በኋላ የሚሆነውን ማን ይነግረዋል? “ መክ.6፡12

የሰው ዘር ሲባል ውስን ነው። እንኳን ከእርሱ በኋላ የሚመጣውን ሊያውቅ ቀርቶ በጊዜው በህይወቱ እየተከናወነ ያለውን ነገር በሚገባ ሳይገነዘበው ያልፋል። ሰው የሚያደርገው ነገር ሁሉ ጊዜያዊ ጥቅም እስከሰጠው ድረስና ጊዜያዊ ስሜቱን እስካረካለት ድረስ ስለሚያስከትለው ውጤት ግድ ሲሰጠው አይታይም።

ትዕቢተኛው ይህ ጸያፍ ተግባሩ የሚያስከትለውን አስከፊ መዘዝ በዓይኑ እስከሚያይ ድረስና ከመጣበትም መዘዝ የተነሳ እስኪያለቅስ ድረስ ከማመንዘር የሚመልሰው የለም። ሰካራሙ ትዳሩ፣ገንዘቡና ሰውነቱ በመጠጥ ብርታት ተበልቶ እስከሚያልቅና በድንገት ባዶ ሆኖ ራሱን እስኪያገኘው ድረስ “አትስከር” ብለው በሚመክሩት ላይ ሲያፌዝ ይኖራል። የሚበጀውን የሚያውቅ ሰው ጊዜያዊውን ብቻ ሳይሆን ለዘላለም ቤቱ ያስባል። ስለዚህ ከዛሬ ደስታ ይልቅ ዘለቄታዊ እውነትን ይመርጣል።